፪. ወደ ውጭ አገር የሚላከው በመስክ ላይ እያለ ምርመራና ቁጥጥር የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ለመስክ ቁጥጥር በቀን ........................ ብር ፳

፫. ወደ ውጭ አገር የሚላከው ሕክምና የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ሕክምናው በትክክል መከናወኑን ለመቆጣጠር በሰዓት ........................ ብር ፲፭

፫. <u>ስለሚወገዱ ዕፅዋት</u>

፩. አንድ ዕፅዋት እንዲወገድ በተወሰነው መሠረት የማስወገድ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ተቆጣጣሪው በቦታው ተገኝቶ ለሚያደርገው ክትትል በሰዓት ........................ ብር ፲፭

፪. ዕፅዋቱን ለማስወገድ የሚያስፈልግ የመጓጓዣ ፣ የሰው ጉልበትና ሌሎች ወጪዎች የሚሸፈኑት ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ይሆናል ።

2. If export item requires active growth inspection while at the field, field inspection fee

Per day .... .... .... .... .... Birr 20.00

3. If export item requires treatment. supervision fee per hour .... .... .... .... .... .. Birr 15.00

3. *Disposal*

1. If import and/or export consignment is decided to be disposed. supervision fee per hour .... Birr 15.00

2. All transport and labour costs required during disposal will be covered by the importer or exporter.